# 16. ጌዴኦ



የመጀመሪያዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ተማሪዎች

አቶ ወራሳ፡ አቶ ጌዴዎ፡ አቶ ሹንቴ፡ አቶ ዳካ ሴሬ



ዲላ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን (በኢትዮጵያ ትልቁ የቤተ ክርስቲያን አዳራሽ)

# በጨለመበት በራ

በጨለማው ዘመን በጨለማ የሚኖር ሕዝብ ነበር በመንፈስም፥ በሥጋም። የጌዴኦ ሕዝብ ለዳግማዊ ምኒልክ እንደራሴ ለደጃዝማች ሉልሰገድ አጥናፍ ሰገድ ከገበረ በኋላ ነበር ለመሐል አገር አመለካከት የተከፈተው። ከደጃዝማች ሉልሰገድ በኋላ የተሾሙት ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ ለማእከላዊ መንግሥት የጦርና የሲቪል ሰፋሪዎች መተዳደሪያ ይሆን ዘንድ የሲዳሞን መሬት ሁሉ እያስለኩ አደሉት። አገሬው ከርስቱ ተነቀለ።[1]

የኑሮ ቀምበር የከበደበት ሕዝብ ርስቱን መነቀሉ አንሶት ለጦርና ለሲቪል ሹማምንትና ሰፋሪዎች ነፃ የጉልበት አገልግሎት የመስጠት ግዴታም ነበረበት። በተወካይ ባላባቶቹ በኩል አቤቱታ ለማቅረብ ሲሞክር በተወካዮቹ ላይ እንግልትና የአደባባይ የጅራፍ ቅጣት እየተፈጸመባቸው ለእስራት ተዳረጉ። ከዳግማዊ ምኒልክ እረፍት በኋላ የነበረው ወቅት በማዕከላዊ መንግሥት ውስጥ የሥልጣን ያለመረጋጋትና የሥልጣን ባዶነት የነገሠበት ጊዜ በመሆኑ የሕዝቡ እምባ ሳይታበስ የጣሊያን ወረራ ተከተለ።

ከ1928–1933 ዓ.ም. ድረስ በነበረው የፋሽስት ጣሊያን ወረራ ዘመን በሌላውም የደቡብ ኢትዮጵያ ክፍል እንደ ተደረገው አገሬው የተነጠቀውን መሬት መልሶ ወሰደ።

ጣሊያኖች ከተባረሩ በኋላ ደግሞ የቀድሞ ሠፋሪዎች መልሰው ባለመሬት ሲሆኑ አገሬው ገባርና ጢሰኛ ሆነ። ሕይወት መራር ሆነች። እንዲያም ሆኖ መሬታቸው እንዲመለስላቸው፥ እንደማንኛውም ዜጋ የሚያስፈልገውንም ግብር ለመንግሥት ብቻ እንዲከፍሉ አቤቱታ ማቅረባቸውን አልተውም ነበር። በመጨረሻም መላ አድርገው የቀየሱትን ዘዴ አንድ ጸሐፊ እንደሚከተለው አርገው አቅርበውታል፦

---

[1]. ላጺሶ. ጌ. ድሌቦ 1983 ገጽ 170

*የጌዴኦ ሕዝብና ባላባቶቻቸው በየጊዜው የሚሾሙ ገዢዎች ከጉልተኞች ጋር በመተባበራቸው መሬታቸው ተነጥቆ መቅረቱንና ለወደፊትም አቤቱታቸው የማይፈጸም መሆኑን በልምድ በማወቃቸው ባላባትነቱን ለመንግሥት ቢያስረክቡ መንግሥት ወዲያው መሬታቸውን የሚያስመልስላቸው መሰላቸው። ስለዚህ በሕዝብ ስብሰባ ተነጋግረውበት ባለቤትነቱን ለቤተ መንግሥት ለማውረስ ወሰኑ። ውሳኔውንም በጊዜው የነበረው ባላባት ባለምባራስ አሰፋ ጭምቡሮ እንዲያስፈጽም ተደረገ።*

*በዚሁ የሕዝብ ውሳኔ መሠረት የጌዴኦ ባላባትነት ለልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለ ሥላሴ ተሰጠ። ልዕልቲቱም በደስታ ተቀበሉት። ነገር ግን ልዕልት ተናኘ ወርቅ ኃይለሥላሴን ከሌላ የሲዳማ ጉልተኞችና የመንግሥት ባለሥልጣኖች (ባለቀላድ) ለይቶ ማየቱ የሕዝቡ የዋህነት ብቻ ነበር። ነገሩ ከድጡ ወደ ማጡ መሆኑ ውሎ ሳያድር ወዲያውኑ በግልፅ ታወቀ።*[2]

ልዕልት ተናኘ ወርቅ ከጌዴኦ መሬት የባላባትነት የአንበሳ ድርሻቸውን 500 ጋሻ መሬት አንስተው ሌላውን ለመደብ አጋሮቻቸው ተውት፥ የሕዝቡ ብሶትና ጩኸት ቀጠለ።

ገባሩና ጪሰኛው ምንም እንኳን ከእለት እንጀራው የሚተርፍ ጥሪት ባይኖረውም አልፎ አልፎ ኑሮአቸውን ያሸነፉ ገበሬዎች ቆርቆሮ ቤት ለመሥራት፥ ቦላሌ ለመልበስ፥ ጠብመንጃ ለማንገት፥ ጩቤ ለመታጠቅ ቢፈልጉ እንኳን ባለቀላዶቹ አይፈቅዱላቸውም ነበር።ቀንበሩ አእምሮአዊና አካላዊም ነበር።

የሕዝቡን የእለት ተእለት ሕይወት ያጨለመው አስተዳደራዊው የብረት ቀንበር ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊው እስራትም ጭምር ነበር። እንደማንኛውም ኋላ ቀር አውራጃዎች አዝመራ፥ እንስሳት፥ ሕዝብ የሚፈጅ ወረርሽኝ በየወቅቱ እየተነሣ አገዛዙ ያነሳቀለውን ሕዝብ ትክሻ የበለጠ ያዳክመዋል።

በአንድ የሕይወት ዘመን፤ በአንድ ጊዜ፥ ከአምላኩ(መገኖ) ከገዥዎቹም ይጣላል። ገዢዎቹን፥ የገዛ ንብረቱን ሰጥቶ፥ ላቡን አፍስሶ እንደሚለማመጣቸው

---

[2] .ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 172

“የሩቅ አምላኩን” መገኖንም እንዲሁ ለመለማመጥ( ለመለማመን) አቅሙ የማይፈቅድለትን ሁሉ ከአቅሙ በላይም ያደርጋል።

አማልክቱ ከሚገለጡባቸው ውቃቢዎች መካከል ሺፎ መገኖ፥ አዳዮ መገኖ፥ ጎላማ መገኖ . . . ወዘት የሚባሉት ጥቂቶቹ ናቸው። ሥርዓተ አምልኮ መፈጸም በተገባ ጊዜ የዚህ ዓይነቱን ጉዳዮች ለሕዝብ ጆሮ የማድረስ ኃላፊነት ባለባቸው “ ሃይቻ” በተባሉ ባህላዊ ሹማምንት በኩል አዋጅ ተለፍፎ የቄጣላ በዓል ይዘጋጃል። ሕዝቡም ገዳ፥ ሮጋ፥ ጀዕልቀባ፥ ጄልቀባ በተሰኙ የሥልጣን እርከኖች በተቀመጡ ሹማምንት አስተባባሪነት “መገኖን” በዜማ እየተለማመነ ወደ ተመረጠለት የአድባር ቦታ ይሰበሰባል። " መገኖ ማሪ ! ! መገኖ ማሪ ! ! " አምላክ ሆይ ማረን . . . ! የዜማው አዝማች ነው።

በተመረጠው የአድባር ቦታ መሰዊያ እና የመሰዋዕቱ በግ ይዘጋጃል ። የበጉ መልክ ጥቁር መሆን አለበት፤ በጉ ከመሰዋቱ በፊት አንድ ጆሮው ይቆረጣል፥ አንድ ዓይኑ ይጠፋል፥ አንድ እግሩ ይሰበራል። ኋላም አንገቱ ሳይቆረጥ በመሰዊያው ላይ በነደደው እሳት ውስጥ ከነነፍሱ ይወረወራል። « በአንካሳ መስዋዕት» መገኖም ከቁጣው ይመለሳል፤ ዝናብ ጠፍቶ ቢሆን ይመጣል”፤ በሽታ ከፍቶ ቢሆን ጤና ይሆናል፤ ጦርነት አስፈርቶ ቢሆን ሰላም ይወርዳል፤ ይባልለታል። ይህ ሥርዓተ አምልኮ ቄጣላ ይባላል።

ሥርዓተ አምልኮው(ቄጣላ) የሚደረገው ከላይ የተጠቀሱት አደጋዎችና መቅሰፍቶች በአጋጠሙ ጊዜ ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ ለአማልክቱ ክብር፥ አልፎ አልፎም የዕድል ፈንታ ነጋሪ አእዋፍን ድምጽ በመስማትና ለይቶ በመተርጎም ነው። ጌዴኦ ኢትዮጵያ ውስጥ ወደር የሌለው ለምለም ምድር፥ በአብዛኛውም በልዩ ልዩ የተፈጥሮ ዛፎች የተሸፈነ በመሆኑ ከፍተኛ የአእዋፍ ክምችት እንዳለበት ቢታወቅም፡- የወፍ ቋንቋ አዋቂዎች፡- ጦጥሳ፥ ኡሩንጎ፥ ፍንጫአ፥ ስንብራ፥ ሁዕሳት

በጆኦ . . . ወዘተ ለሚባሉት የአእዋፍ ዝርያዎች “ ንግግር” ትኩረት ይሰጣሉ።

የተሰማው የወፍ ድምፅ ትርጓሜ ክፉ አደጋን የሚያመላክት ከሆነ ያ የተነገረለት ሰው ወራሞ(በጹቄት መልክ የተዘጋጀ ቆጮ) ጠቀም አርጎ ወስዶ በቤቱና በቅጥሩ ዙሪያ ይረጭና የወፉን ስም በመጥራት፡- “ አባክህ ይህን ብላና እኔን ተወኝ . . . ከእኔም ተመለስ! ክፉ ነገርህን ይዘህ ሂድ . . !.” ይለዋል። በመሠረቱ የሚጠራው ወፉን ቢሆንም መልእክቱ ግን ወፉን ለላከው መንፈስ ነው። ከዚህም የሚብስ አለ።

በወፉ ድምፅ ትርጓሜ የደነገጠ ሰው፡- የወፍ ጎጆ፥ ደረቅ ጥሾ ( ከእንሰት የሚገኝና ገመድ ለመሥራት የሚያለግል ልጣጭ ) የደረቀ አጥንት፥ የሸረሪት ድር፥ . . . እነዚህን ምናምንቴ ነገሮች ሰብስቦ ከግቢው አጥር ውጭ ይሄዳል። ከአጥሩ በር በስተቀኝ በዛ ያለ ማገዶ የተማገደበት እሳት ያነዳል፤ በግራ በኩል ደግሞ አነስ ያለ እሳት ያነዳል። ከዚያም የቤተሰቡ አባላት በውጭ ይሰበሰቡና በአባት( በቤተሰቡ ኃላፊ) መሪነት በእሳቱ ዙሪያ እየዞሩ አማልክቱ የላኩባቸውን ወፍ ስም እየጠሩ . . . “ ተው . . . ከኛ . . . ተመለስ ! !” ይላሉ፥ በዜማ አምልኮአቸው ከተሰማ ወፉ ይዞት የመጣው አደጋ ተመለሰ ማለት ነው። እኒህንና እኒህን የመሳሰሉ በቤተሰብና በግለሰብ ደረጃ የሚደረጉትን ሥርዓተ አምልኮዎች የሚያልፍ ነገር ሲመጣ ነው ቂጣላ የሚዘጋጀው።

ቂጣላ ከሚዘጋጅባቸው አብይና አንዱ ምክንያት የሞት መልአክን ለማባረር ነው። የሞት መልአኩ “ ጌላ ” ይባላል። ጌላን በዓይኑ ያየ ማንም የለም። ግን አዋቂ ነን የሚሉት በአፈ-ታሪካቸው የቁመናውን ምስል፥ ክፋቱንና ተግባሩን ይተርኩለታል። በዓይን ጎሊናቸውም ይስሉታል።

ጌላ አንድ እግርና አንድ እጅ ብቻ ያለው ነገር ግን በአንድ ቦታ ያልተወሰነ አስፈሪ የሞት መልአክ ነው። በአፈ ታሪኩ እንደሚነገረው ጌላ የሰዎችን ስም ዝርዝር የሚይዝበት መዝገብ አለው። እርሱ

የሚፈልገውን ሰው በመዝገቡ ሲጠራ ያ ሰው ያቺን ቀን አያልፍም፥ ይሞታል። ጌላ ደስታ የሚሆንለት እንዲህ ሰዎችን በሞት ሲሰበስብ ነው።

በተለያየ ምክንያት ሞት ሲበዛ፡— የጌላ አድራጎት መጠኑን አልፎአል ማለት ነው፥ ስለዚህም የሞትን መልአክ ለማባረር የቁጣላ በዓል ይዘጋጃል። በበዓሉ ላይ የጌዴኦ ወጣቶች ወንዱም ሴቱም ተሰባስበው ጦርና ጋሻ በመያዝ በባህላዊ ዘፈንና ጭፈራ ከአገራቸው ያባርሩታል።

የወንጌል ብርሃን ከመብራቱ በፊት ሕይወት በጌዴኦ እንዲህ ከባድና " ረቂቅ " ነበረች። ረቂቅነቷ አለመጨበጧ፥ መላ ማጣቷ፥ ትርጉም ማጣቷ ነው። ክብደቱም ቀንበሩ ሰይጣናዊ በመሆኑ ነው።

## እውነተኛው ብርሃን

እንደ አብዛኛዎቹ የደቡብ አውራጃዎች ሁሉ ባህላዊ ትንቢተኞች በጌዴኦና በጉጂ ማኅበረሰቦች የሕይወት መታደስ እንደሚሆንላቸው ተንብየው እንደነበር ያስታውሷል።[3] ከእነዚህ መካከል አቶ አታራ ገመዶ በጌዴኦ እና አቶ ቢከማ ጋልጎ በጉጂ የታወቁ ቅድመ ወንጌል ትንቢተኞች ሲሆኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ለጌዴኦና ለአካባቢው ሕዝብ ወንጌልን በመስበክና በመልካም ክርስቲያናዊ አርአያነታቸው የሚነሱት ሚ/ር አልበርት ብራንት ሦስተኛውን ሰው በባለ ራእይ ማእረግ ነው በመጽሐፋቸው ውስጥ ያስቀመጡት። ሰውዬው የያኔው ጎልማሳ ይህ ጽሑፍ በሚዘጋጅበት ወቅት ደግሞ በሰማኒያዎቹ የእድሜ ክልል ያሉት አቶ ወራሳ ወንጌ ናቸው።

አልበርት ብራንት እንደሚሉት ወራሳ ወንጌ ራእዩን ያዩት በ1933 ዓ.ም. አካባቢ ነበር። በራእያቸውም ሚስዮናውያን ሄደው ለመጀመሪያ ጊዜ የሠፈሩበትን ቦታ፥ ለመጀመሪያም ጊዜ ወደ ቦታው የሄዱትን ሚስዮናውያን ብዛት፥ ያደረጉትን የፀሐይ መከላከያ ባርኔጣ፥ በእጃቸው የሚይዙትን የመጽሐፍ ቅዱስ የሽፋንና የጠርዝ ቀለማት ሁሉ

---

[3]. ወንድዬ ዓሊ 1990 ገጽ 74–75

ነበር። በራእያቸውም ሳሉ ሌሊት ይሁን ቀን፥ በኀልም ይሁን በውን ለይተው ባልተረዱት ሁኔታ ፈጣሪያቸው " መገኖ " የእኔን መንገድ የሚያሳዩህ ሰዎች እኒህ ናቸው አላቸው።[4]

ወራሳ ወንጌ ላዩት፥ ራእይ ትርጉም ሳያገኙለት ዓመታት አለፉ። ከስምንት ዓመታት በኋላ ግን ጌዴኦንና የአካባቢው ሕዝብ በወንጌል ለመድረስ እና አመቺ ጣቢያዎችን ለመቆርቆር በሚ/ር ግሌን ኬይን የተመራው ሦስት አባላት ያሉት ቡድን ዲላ ደረሰ። ወራሳ በኀልማቸው ባዩት ቦታና የሾላ ዋርካ ሥር ድንኳን ተከለ፤ ዕለቱ የገበያ ቀን ስለነበር ወራሳ ወንጌ ወደገበያው ቦታ ሲሄዱ አዩት። የራእዩ ትርጓሜ ነፍስ ዘራ። የቡድኑ አባላት ግን ብዙም ሳይቆዩ ወደ ቡርጂ ወረዱ ተመልሰውም፤ ወደ አዲስ አበባ ሄዱ። ከጥቂት ወራት በኋላ ጥር 25 ቀን 1941 ዓ.ም. ( ፌብራሪ 2 ቀን 1949 ) ሚስዮናዊው አልበርት ብራንት ዲላ ደረሱ። በጊዜው የከተማ ዳርቻ በነበረው ቆፌ ላይ ሠፈሩ። የትምህርት ቤት፥ የክሊኒክ፥ የመኖሪያ ቤት ግንባታ ሥራ ወዲያው ተጀመረ። በእጅ መዘውር የሚሠራ ቴፕ በቆፌ መንገድ ዳር አስቀምጠው አጫጭር ስብከተ ወንጌሎችን ለተላለፈው መንገደኛና ገበያተኛ ማሰማት ጀመሩ። ባለቤታቸው ኤቪሊን ከተመደቡበት አድካሚ የሕክምና ሥራ ጎን ለጎን የመሠረተ ትምህርት መስጫ ክፍል አዘጋጁ። የመጀመሪያው የጌዴኦ ቤተ ክርስቲያን አማኝና ፊደል ቆጣሪ ባለትዳርና በጊዜው የስድስት ልጆች አባት የነብሩት አቶ ወራሳ ወንጌ ሆኑ፤ አንድ።

ሚስዮናውያኑ ሥራቸውን ተረጋግተው ቀጠሉ። መድኃኒት ፍለጋ፥ ፊደል ለመቁጠርና፥ ሥራ ለመቀጠር ወደ ቆፌ የሚመለሱት ሰዎች ቁጥር ተበራከተ። አቶ ዳካ ሴሪ ግን ከሁሉም በላይ የሳባቸው በውስጣቸው ያደረው የትምህርት ናፍቆት ነበር። ዳካ የጌዴኦ ተወላጅ ቢሆኑም የሚኖርት በጉጂዎች መካከል ስለነበር የጉጂዎችን ባህልና ቋንቋ በሚገባ የተለማመዱ ሰው ነበሩ። አቶ ዳካ በአብያታ ሐይቅ ዳርቻ

[4] . Barant, Albert E. 1992 p.2-5

ከጉጂ ወዳጆቻቸው ጋር የሚያሳልፉትን ቀናት እየቀናነሱ በቆፌ የሚሰዮን ጣቢያ ቋሚ የፊደል ተማሪ ሆኑ።



*አልበርት ብራንትና ኤቭሊን ብራንት*

በ1942 ዓ.ም. አጋማሽ ላይ ተማሪዎች በክፍላቸው ውስጥ ሆነው አስተማሪያቸውን ሲጠባበቁ አልበርት ብራንት፡- መጽሐፍ ቅዱስ ከሰል፥ ውኃ የተሞላ ባልዲ፥ ማስታጠቢያ፥ ፎጣ፥ ሳሙና እና መስታወት ይዘው ገቡ። ነጭ ሸራ ጫማ፥ ነጭ ቁምጣና፥ ነጭ ሸሚዝ ለብሰው ነበር። በተማሪዎቻቸው ፊት ቆመው የለበሱትን ነጭ ልብስ፥ ፊታቸውን፥ ጫማቸውን ሁሉ በከሰል ቀቡ። ቀጥሎም ዮሐንስ 3፡16 በማንበብ ስለ ኃጢአት እና በኃጢአትም ምክንያት በሰው ልጅ ላይ ስለተፈረደው ሞት ሰበኩ። . . . ሰውዬው ምን ነካቸው? በማለት ተማሪዎቻቸው ፈዘው ይመለከቷቸው ነበር። በስብከታቸው አጋማሽ መስታዋቱን አንስተው ፊታቸውን ሲያዩ ቀድሞ ምንም እንደማያውቅ ሰው ኡ! ኡ! ! . . . ብለው ጮኹ። ምን ነው ሳትነግሩኝ?. . . እንዲህ ሆኜ ፊታችሁ ስቆም ለምን ዝም አላችሁኝ?! በማለት ተማሪዎቻቸውን ጠየቁ። ቀጥሎም በያዙት ውኃና ሳሙና ታጠቡ። በፎጣ አደረቁ። ልብሳቸውን አራግፈው



አልበርት ብራንትና ኤቭሊን ብራንት

ሌላ ልብስ ቀየሩ፤ ዳግም ፊታቸውን በመስተዋት አዩ። በፈገግታ " የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻል" በማለት ሰበኩ።

ከዚህ ስብከተ ወንጌል በኋላ የተከተለውን ውጤት አቶ ዳካ ሲመሰክሩ፡—

*. . . ኃጢአታችን ታየን፥ ብዙ ተጨንቀን ስናስብ ደግሞ የኃጢአት ማምለጫውን አሳዩን። . . . እኔ በግሌ ልቤ እንደ ውኃ ፈሰሰ። በዚያን ቀን ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝ አድርጌ ተቀበልኩ። የውስጥ ዓይኖቼ በሩ። ብዙም ጊዜ ሳልወስድና መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ሳላጠና በውስጤ ከተቀጣ*

*ጠለው የአዲስ ሕይወት*



*አቶ ዳካ ሴሪ*

*እውነት የተነሣ በየገጠሩ እየዞርኩ " በጌታ በኢየሱስ እመኑ. . . ! ንስሐ ግቡ ! " እያልኩ ቆላ ቆላውን ማወጅ ጀመርኩ። አቶ ወራሳ ወንጌም እንዲሁ እንደኔ አድርገቸው የጌታን ስም እያወጁ በሌላ አቅጣጫ( በይርጋ ጨፌ) መዞር ጀመሩ። እግዚአብሔር የሕዝቡን ልብ ነክቷልና ዘሮቻችን፥ ጎረቤቶቻ ችንና፥ ወዳጆቻችን ሁሉ ክርስቶስን ወደ ማወቅ እውነት ዘወር አሉ። ክርስቶስን ያመነው ሰው ባመነበት* በዚያው ዕለት ከአንዱ ቀበሌ ወደ ሌላው እየተዘዋወረ « ኢየሱስ ያድናል! *ንስሐ ግቡ! » በማለት ያገኘውን ደስታ ይመሰክር ነበር።*

አቶ ወራሳ እና ከአቶ ዳካ ሌላ ሽፈራው ዋቆ፥ ኩርሴ ጎቻ፥ ሾንጤ ጎቻ፥ በራሶ ሹርዷ አምነው ሁሉም በየቀበሌአቸው መስበክ



ጀምረው ነበር፤ ለዓይነተኛው የመንፈሳዊ ሥራ መስፋፋት እንደምልክት የሆነው የቀድሞው ባለውቃቢዎችና ባህላዊ ትንቢተኞች– እነ አቶ አታራ ገመዴ ሌሎችም በብዛት ወደ ቤተ ክርስቲያን መጨመራቸው ነበር።

በቀደመው የጌዴኦ ልማድ " ውቃቢ" የሚባለው ነገር ለባለውቃቢውም ሆነ ውቃቢው ለነገሠበት የአገሬው ሕዝብ" ይህን አምጣልኝ !. . . ይህን ገብርልኝ. . . ያንን ሰዋልኝ . . . ! ይህን ካላደረግህ እንዲህ ይደርስብሃል፥ እንዲህ ያለ አደጋ ይመጣብሃል. . . ! እያለ ሲያስፈራራ እንጂ ወደ ሚጠቅም እና ከእርሱ ወደተሻለ ነገር ሲመራ አልታየም ነበር።

አታራ ገመዴ ግን ዘመኑ በተፈጸመ ጊዜ ከአስር ዓመት በፊት በምልክት ያናገራቸው መንፈስ በ1943 ዓ.ም. መጥቶ የዘንባባውን መብቀል፥ አስገንዝቦ ወደ ቆፌ እንዲወጡ አስገደዳቸው( በመከራ ውስጥ ያበበች ቤተ ክርስቲያን ገጽ 73–74 )። ሄደውም ከአልበርት ብራንት ጋር ተገናኙ። ታሪካቸውን ነገሩአቸው። አልበርት ደግሞ የክርስቶስን ወንጌል መሰከሩላቸው። በንስሐ ጸሎት ወደ እምነት መሯቸው። ስለዚያች ቀን እንዲህ ይላሉ፡–

*"ከዚህ በኋላ እንደቀድሞው ዘመን የሚያስጨንቅ የውቃቢ መንፈስሳይሆን የእግዚአብሔር መንፈስ ወረሰኝ፤ ለራሴ እስከሚገርመኝ ድረስ፥ በምን ምክንያት ደስ እንደሚለኝ እንኳን ሳላውቅ ውስጤ የማያቋርጥ ደስታ ፈሰሰ።"*



አታራ ገመዴ





አታራ ገመዴ

አቶ ወራሳ ወንጌ፥ አቶ ዳካ ሴሪ፥ አቶ አታራ ገመዴ እኒህ ሦስቱ በጌዴኦ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ሥራ እግዚአብሔር እንደ እርሾ የተጠቀመባቸው ናቸው። ሚስዮናዊው አልበርት ብራንት ስለ ጌዲኦ ቤተ ክርስቲያን በጻፉት መጽሐፍ እንዲህ ብለዋል፡-

> *ስለ ወራሳ፥ ዳካ እና አታራ እግዚአብሔርን ሁል ጊዜ አመሰግነዋለሁ! እነዚህ ሦስቱ እንደ ጴጥሮስ ያዕቆብና ዮሐንስ እግዚአብሔር ለሥራው ሲል ከወገኖቻቸው መሐል መርጦ አእማድ አድርጎ ያቆማቸው ናቸው። እነዚህ ሦስቱ የእግዚአብሔር መንጋ ጠባቂና እንደ ባለ አደራ የሚታዩ ናቸው። 500,000 ከሚሆነው በዙሪያቸው ካለው ሕዝብ መካከል እነዚህ ሦስቱ እና ሽፈራው ዋቆ ናቸው ለመጀመሪያ ጊዜ የጥምቀት ሥነ ስርዓት የፈጸሙት።*[5]

## አጥቢያ ተከላ

በ1944 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ አልበርት ብራንትና ቤተሰባቸው ለእረፍት ወደ ካናዳ ሄደው በነበሩበት ወቅት ከቀዳማይ አማኞች መካከል አንዱ የሆኑት አቶ በራሶ ሹርዲ በሚኖሩበት ቀበሌ ያሉትን የወንጌል አማኞች አሰባስበው በራሳቸው ግቢ ውስጥ አንድ ጸሎት ቤት ሠሩ። በዚያች ጎጆ ቤት ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ባሉት የተመረጡ ቀናት መጽሐፍ ቅዱስ ማጥናት፥ መዘመር፥ መጸለይ ጀመሩ። ጅማሬውም በጌዴኦ ምድር አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትን የመትከል የመጀመሪያው አገረሰባዊ መነሳሳት ሆነ። ሚስዮናዊው ከእረፍታቸው ሲመለሱ በሰሙት ነገር በመገረም የጎላን አማኞች ኅብረት በመጎብኘት የአገሬውን ሰዎች መነሳሳት አደነቁ፥ ጎላም የመጀመሪያዋ የጌዴኦ ቤተ ክርስቲያን አጥቢያ ሆነች። እሷም አሁን ላሉት 400 ያህል የተመዘገቡና ያልተመዘገቡ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ሁሉ እናት ሆነች።

---

5 .Ibid

በጎላ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሲተከል የጨለማው ገዢ ዝም ብሎ አላየም። በመጀመሪያ ባለውቃቢው የአቶ ቦራሶ አባት በባህላዊ ውግዘትና እርግማን የአካባቢውን ሕዝብ በማስተባበር በልጃቸውና በሌሎች አማኞች ላይ ተነሡባቸው። ብርቱ ጸሎትና ምልጃ ተደረገ። በብዙ ትዕግሥት የታጀበ ስብከተ ወንጌል ተካሄደ። ባለውቃቢው አሳዳጅ ከተቃዋሚዎች



አቶ በራሶ ሹርዲ

ጎራ ወጥተው በወንጌል አመኑ። ለአጋንንት አሠራር የመለየታቸው ምልክት የሆነው ረዥም ጠጉራቸው ተላጨ፥ በጣታቸው ላይ ያደረጉት በርካታ ብረታብረት ወለቀ፥ የአምልኮተ ጣዖት መገልገያ ቁሳቁሶች፥ ተቃጠሉ፥ ነጻ ወጡ።

ሌላው ተቃውሞ የተነሣው በባለቀላዶች ግፊት ነበር። የጎላ ባለቀላድ ወ/ሮ ዘነበች የመጀመሪያዋን አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ያለ ፈቃዴ በርስቴ ላይ ሠርታችኋል በማለት ከአሽከሮቻቸው ጋር በመሆን ጎጆ ቤቷን አፈረሱ።[6] አቶ በራሶን ጨምሮ ስድስት ሰዎች ተከሰው ወደ ወኅኒ ተጣሉ።

ሚስዮናዊው አልበርት ብራንት ከሌሎች ሚስዮናውያን የሚለዩበት አንዱ ነጥብ በጊዜው በነበረው የባለርስትና ጪሰኛ ጭቅጭቅ ምክንያት በአብዛኛው ገባርና ጪሰኛ የነበሩት አማኞች በተለያየ ሰበብና መነሾ ወደ ወኅኒ ሲጣሉ ፈጥነው በመድረስ ስንቅ በማቀበላቸው፥ አልፎ አልፎም በጠቅላይ ግዛትና በብሔራዊ ደረጃ አቤቱታቸውን በማሰማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጋቸው ነው። እነ አቶ በራሶ በታሠሩ ጊዜ ስንቅ በማቀበልና አቤቱታቸውን ለባለሥልጣናት በማቅረብ ያደረጉላቸውን

---

[6] . በራሶ ሹርዲ፥ ቃለ ምልልሳዊ መረጃ፥ ነሐሴ 7 ቀን 1988 ዓ.ም. ዲላ፥ጌዴኦ።



*አቶ በራሶ ሹርዲ*

ውለታ አዛውንቶቹ የወንጌል ሰዎች እስከአሁን ድረስ የሚያስታውሱት ትዝታ ነው።

የጎላ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ ማማር አማኞች ባሉበት ገጠሮች ሁሉ የጸሎት ቤቶች እንዲከፈቱ የአገልጋዮችን መንፈስ አበረታታ። ከአገሬው መካከልም አቶ ወራሳ ወንጌ የመጀመሪያው ወንጌላዊ በመሆን ሙሉ ጊዜያቸውን ለጌታ ሥራ ሰጡ። ዳካ ሴሪ በጉጂዎች መካከል ያለመቆጠብ ወንጌልን አገለገሉ፥ የሺፎ መገኖ ውቃቢ ዋና ባለሟል የነበሩትና በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ ተሰሚነትና አክብሮት የነበራቸው አታራ ገመዶ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሙላት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መስበክ በመጀመራቸው ባመኑት ላይ በርካታ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ተጨመሩ። ምእመናን በቁጥር በመበራከታቸው ከቤተ ክርስትያን ውጭ የሚደርስባቸውን ተጽእኖ ለመቋቋም እርስ በርስ ተቀራርበው የሚደጋገፉበትን ስልት ቀየሱ፤ የሰባ ዓመቱ አዛውንት አቶ በራሶ ሹርዲ በጊዜው ስለነበራቸው ሕብረት እንዲህ ይላሉ፦

> *. . . ክርስትናችን እንግዳ የሆነባቸው. . . ሲቃወሙን እኛ እርስ በርስ ተጠጋጋን፤ በየቀኑም ኅብረት ማድረጋችንን ቀጠልን። ኅብረት የምናደርገው በጣም ትንሽና ቀላል በሆነ መንገድ ነው። የጸሎት ቤታችን ጎጆ፥ ግድግዳው አገዳ፥ ክዳኑ ሳር፥ ምንጣፉ ሰሌን፥ የምንጠጣው ቡናና ቁጢ፥ ቁርሳችን ንፍሮ፥ ደስታችን ግን በብርና በወርቅ አይተመንም ነበር።*[7]

የምእመናን የሕይወት መታደስ በጊዜው ለነበረው ስርዓትና ለባለርስቶች ተጨባጭ በሆነ መንገድ መገለጡን የመጀመሪያው የጌዴኦ ቤተ ክርስቲያን የአውራጃ ማሕበር ፕሬዚዳንት የነበሩት አቶ አታራ ገመዶ ሲናገሩ ደግሞ ፦

> *. . . በወንጌል ምክንያት አእምሮአችን ታደሰ፥ ከባለ ርስቶችና ከገዢዎቻችን ጋር የነበረን ግንኙነት ሁሉ ሌላ መልክ ያዘ። ፊደል ቆጠርን፥ ከነሱ በላይ ተማርን። ሳያውቁት ሳይገልጡት፥ የሚመኩበትን መጽሐፍ( መጽሐፍ ቅዱስ ) ከእነርሱ በላይ አወቅን። ጥያቄዎችንም ማንሳት ጀመርን። . . . ራሳችንን*

---

[7] ዝኒ ከማሁ

*( ሕይወታችንን ) ለመለወጥ በደከምን መጠን እግዚአብሔር ባረከን። መሬታችንን ሲቀሙን እግዚአብሔር ጓሮአችንን ይባርካል፥ የጓሮ አትክልታችንን ሲነጥቁን እግዚአብሔር ጓዳችንን ያትረፈርፋል። ንጹሕ በላን፥ ንጹሕ ለበስን፥ ልጆቻችንን አስተማርን። ወንጌል ሰው አረገን፣[8] ብለዋል።*

የወንጌሉ ኃይል በሕይወት መታደስ፥ በድንቅና በተዓምራት በብዙ ምልክቶችም መጽናቱ የሕዝቡን አትኩሮት ሳበ። በ1945 ዓ.ም. የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተከፍቶ ከታሰበው በላይ ወደ ቤተ ክርስቲያናት የሚጎርፈውን ሕዝብ የሚመግቡ አገልጋዮች ሥልጠና ጀመሩ። የመጀመሪያዎቹ የአራት ዓመት ሠልጣኞች አቶ ወራሣ ወንጌ፥ አቶ ጌዴቻ፥ አቶ ሸንጤ ጎቻ፥ አቶ ዳካ ሴሪ ሲሆኑ ትምህርታቸውን ጨርሰው የተመረቁት በ1949 ዓ.ም. ነበር። በሁለተኛው ዙር የሠለጠኑት ሰባት አገልጋዮች ነበሩ።

በጥቅምት ወር 1945 ዓ.ም. የመጀመሪያው የመንፈሳዊ ሕይወት ማነቃቂያ ኮንፈረንስ ተደረገ። 200 ያህል ሰዎች በእርጋታ ተካፈሉ። በታህሳስ ወር 1945 ዓ.ም. የመጀመሪያው ክርስቲያናዊ ጋብቻ ሥነ ስርዓት ተካሄደ። ሙሽራው ከመጀመሪያዎቹ ተጠማቂዎች መካከል አንዱ የሆነው አቶ ሽፈራው ዋቆ ሲሆን ሙሽሪቷ ደግሞ የመጀመሪያው የጌዴኦ አማኝ የአቶ ወራሳ ወንጌ ልጅ ወ/ት ዱራ ነች። ዱራ ማንበብና መጻፍ የምትችል የመጀመሪያዋ የጌዴኦ ልጃገረድ ነች ይላሉ አልበርት ብራንት።

የአቶ ሽፈራውና የወ/ት ዱራ ጋብቻ ሥነ-ስርዓት አፈጻጸም ድምቀትና ምስክርነት በወንጌል ከማመናቸው በፊት የተጋቡትን ባለትዳሮች አነቃቃ። አሁን በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ስለሆን የጋብቻ ሥነ ሥርዓት እንደገና ይፈጸምልን በማለት አልበርት ብራንትን ጠየቁ። ብራንት ብዛታቸውን ሲጠይቁ 24 ባለትዳሮች መሆናቸውን ተገነዘቡ። እግዚ. አብሔር የቀደመውን መጣመራቸውን የተቀበለውና የሚያከብረው ቢሆንም እንኳን አጋጣሚውን ለወንጌል ምስክርነት ሊጠቀሙበት ወደዱ። ስለ ሆነም ቀን ቆርጠው፥ ሁሉም አምረው ተውበው፥ በቤተ

---

8. አታራ ገመዴ፥ ቃለ ምልልሳዊ መረጃ፥ ነሐሴ 1988 ዓ.ም.

ሰቦቻቸው ታጅበው እንዲመጡ አደረጉ። በተወሰነው ቀን 24 ቱም ጥንዶች በአንድ ጊዜ በጉባኤ ፊት ቆመው ቃል ኪዳናቸውን አደሱ። የአዲስ ሕይወት መዓዛ የጌዴኦን ገጠሮች ሁሉ አወደ።

የጋብቻ ቃል ኪዳን መታደስን ካነሳን ዘንድ ድርብ ጋብቻ፥ ፍቺ፥ መለያየትና ዳግም ጋብቻ እንደሌላው ኋላቀር ማሕበረሰብ ሁሉ በጌዴኦም አስከፊ ማኅብረሰባዊ ችግር ነበር። የመጀመሪያዎቹ አማኞች የዚህ ግዙፍ ችግር ተካፋይ ቢሆኑም በክርስቶስ ወንጌል አዲስ ሕይወትን ከተጎናጸፉ በኋላ በቀደመው የኑሮ ዘይቤአቸው ሊቀጥሉ አልወደዱም። አዲሲቷ ቤተ ክርስቲያንም ከደኅንነት ማግሥት ያለውን የታረመ ሥነ ምግባር ሥራዬ ብላ ማስተማሯን ቀጠለች። በውጤቱም በድርብ ጋብቻ ተጠምደው የነበሩት የመጀመሪያ አማኞች የመጀመሪያዋን ሚስታቸውን ብቻ እያስቀሩ ከተቀሩቱ ጋር የነበራቸውን የባልና የሚስት ግንኙነት በራሳቸው ውሳኔ አቋረጡ። ነፃ የተለቀቁት ሚስቶች ግን ሌላ ባል እስከሚያገቡ ወይንም ራሳቸውን ማስተዳደር እስከሚችሉ ድረስ የቀድሞው ባል አስፈላጊውን የኑሮ ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ኃላፊነቱን ወሰደ ።[9] በእምነትና በአስተሳሰብ የሚመጥናቸውን ወይም የሚመስላቸውን የትዳር ጓደኛ አግኝተው ለማግባት የፈቀዱትንም እንደ ወንድም፥ እንደ አባት በመሆን የቀድሞ ሚስቶቻቸውን የዳሩ እንደነበሩ ታውቋል።[10]

በዚህ ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር ውስጥ ራሳቸውን አስጨክነው ያላለፉት ከአደባባይ አገልግሎት፥ እና ሽምግልና በመሳሰሉት የኃላፊነት አገልግሎቶች እንዳይሳተፉ ይደረግ ነበር። ከሁሉም በላይ በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ተነሣስተው ወደ ቀደመው የድርብ ጋብቻ ባህል የተመለሱትን አማኞች የመጀመሪያዎቹ መሪዎች ጠበቅ ያለ እርምጃ እንዲወስድባቸው በማድረግ ቤተ ክርስቲያን በቅድስና እንድትኖር ያደረጉት ጥረት እርአያነት ያለው ነው።

---

[9] Brant, Ablert. 1992 pp. 196-198

[10] ባልቻ ቦሬ፣ ቃለ ምልልሳዊ መረጃ ነሐሴ 7 ቀን 1988 ዓ.ም. ዲላ ጌዴኦ።

# የባህል ዘለል ወንጌላውያን በጌዴኦ

በየጊዜው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚጨመሩትን ነፍሳት ለመንከባከብ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መከፈቱ እና አገልጋዮች መሠልጠን መጀመራቸው የወደፊቱን የጌዴኦ ቤተ ክርስቲያን ተስፋ ቢያለመልምም ቤተ ክርስቲያኒቱ በየጊዜው ለነበረው የእግዚአብሔር ቃል ረሃብ ምላሽ ለመስጠት የሚበቃ አቅም ገና አልገነባችም ነበር።

ይህንን ጉዳይ በልዩ ልዩ ሪፖርቶች የተረዱት የከምባታና ሃዲያ ቤተ ክርስቲያን የጊዜው መሪዎች አቶ ሰብሮ ወሰሮ፥ አቶ አበበ ቡሼሮ እና አቶ ሽጉጤ ዳዳ በጌዴኦ የሥራ ጉብኝት በማድረግ ከዚህ ቀደም ከላኩአቸው ሁለት ወንጌላውያን በተጨማሪ በ1945 ዓ.ም. አስር ወንጌላውያንን ለማሰማራት እቅድ እንዳላቸው ለጌዴኦ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በማብሰራቸው ጊዜያዊ እፎይታን ፈጠረ።



ወንጌላዊ ኪዳሞ ሜቻቶ



አቶ ዘኬዎስ ኤደሞ



ወንጌላዊ ኬዳም ሜቻቶ



አቶ ዘኬዎስ ኤደሞ

ኤደሞመጀመሪያ ጊዜ የከምባታና ሃዲያ ወንጌላውያን በጌዴኦ የተሰማሩት በ1942 ዓ.ም. ሲሆን እነርሱም አቶ ዶሴ አወነው እና አቶ ዓለማየሁ በለንጎ ናቸው። የከምባታና ሃዲያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጌደኦ የሥራ ጉብኝት አድርገው እንደተመለሱ ደግሞ ወዲያው ያሰማሩአቸው ወንጌላውያን አቶ መናሾ ጫዕሞ እና አቶ ኬዳሞ ሜቻቶ ናቸው። ከእነርሱም በኋላ ሌሎች 11 ወንጌላውያን ተልከው በጌዴኦ የሚያገለግሉት የከምባታ ወንጌላዊት ወንጌላውያን ቁጥር 15 ደርሶ እንደ ነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የከምባታና ሃዲያ ወንጌላውያን በጌዴኦ ሥራ በጀመሩ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ለሕዝቡ ታላቅ መፈታት፥ታላቅ መንፈሳዊ ነጻነት ሆነለት። ከባላባቶች ከባለርስቶችና ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አማኒያን ዘንድ የሚነሣውም ተቃውሞና እሥራት እንዲሁ ቀጠለ። በዚያው ዓመት በተደረገው የመንፈሳዊ መነቃቃት ኮንፈራንስ ተካፋዮች ብዛት አምስት አዳዲስ አማኞችም ወደ ቤተ ክርስቲያን መጨመራቸው ለአዲሲቱ ቤተ ክርስቲያን መሪ አገልጋዮች ብዙ ምስጋና ሆነላቸው።

የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት መብዛት እና የምእመናንን መበራከት ተከትሎ በአውራጃ ደረጃ ማሕበር ለማቋቋም እርምጃ የተወሰደውም በዚሁ በ1945 ዓ.ም. ነበር። በአውራጃ ማሕበር ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የተመረጡት መሪዎች ሊቀ መንበር አቶ አታራ ገመዴ፥ ጸሐፊ አቶ ዳካ ሴሪ፥ ገንዘብ ያዥ አቶ ወራሣ ወንጌ ነበሩ። የጌዴኦ ቤተ ክርስቲያን ከነበራት እድገትና መስፋፋት አንጻር የወንጌል አማኞች አንድነት ማሕበርን ከአቋቋሙት ቀደምት ቤተ ክርስቲያን አንዷ መሆኗ ይታወቃል።

የጌዴኦ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ወንጌልን በመቀበላቸው ለነፍሳቸውና ለሥጋቸው የደረሰላቸውን በረከት ለሌላው የማስተላለፍን ኃላፊነት በአውራጃ ደረጃ መፈጸም የጀመሩት በ1949 ዓ.ም. ነበር። የመጀመሪያዎቹ የጌዴኦ ቤተ ክርስቲያን ባህል ዘለል ወንጌላውያን የተሰማሩት በሐረርጌ ክፍለ ሐገር በጨርጨር አውራጃ ሲሆን እነሱም አቶ ወራሣ ሆቆጠ እና አቶ ገበየሁ ሻሎ ይባላሉ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ

በተለያዩ ክፍለ ሐገራት የሚያደርጉትን ስምሪት ሳያስተጓጉሉ በመቀጠል የስብከተ ወንጌል ራእያቸውንም በአገር አቀፍ ደረጃ ለኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተክርስቲያናት ሁሉ በማጋባት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማድረግ አንጻር መሪዎቿ ሰፊ ተሞክሮን አካብተዋል። ከዚሁ ጋር ወንጌልን ከክልላቸው ውጭ ለመስበክ በተሰማሩበትና፥ ሥፍራ በተቃዋሚዎች እጅ የተገደሉትን እንዲሁም በደረሰባቸው ሕመምና ጉስቁልና ሕይወታቸው ያለፈውን በርካታ የጌዴኦ ወንጌላውያን አስታውሶ ማለፉ አግባብነት አለው።

በጌዴኦና በቡርጂ መካከል የሚገኘው የይርጋጨፌ አካባቢ ከጌዴኦ ጥቂት ዘግይቶ ስብከተ ወንጌል የጀመረ ቢሆንም ታላቅ መስፋፋት የታየበት ከ1945 ዓ.ም. በኋላ ነው።

## ከደቡብ ወደ ደቡብ ጠረፍ

ሚስዮናዊው አልበርት ብራንት እና ባልደረቦቻቸው በቅድሚያ ሥራ የጀመሩት በጌዴኦ ቢሆንም ከአንድ ዓመት በኋላ በ1943 ዓ.ም. በቡርጂ የገምቦ ጣቢያን ከፈቱ። አብረዋቸውም አቶ ገነበ ጋጋ፥ አቶ ኩማ ጋቲሶ የሚባሉ ወንጌላውያን ከወላይታ ቤተ ክርስቲያን በመምጣት የምሥራቹን ቃል ለሕዝቡ አበሰሩ። ከአገሬው ተወላጆችም መካከል እነ አቶ ማሬ ዳያ፥ አቶ ሴኮ ጋዶ፥ አቶ ሶዴ ዳቃ እና ሌሎችም ሰዎች ከነቤተሰቦቻቸው በወንጌል አመኑ። የሥራው መስፋፋት ተጨማሪ የወንጌል አገልጋዮችና መጋቢዎች እንዲሰማሩ ግድ ስላለ የወላይታ ቤተ ክርስቲያን አራት ወንጌላውያንን ለሁለተኛ ዙር ተልዕኮ አሰማራች።

የምእመናን ቁጥር ሲበራከት በመጀመሪያው የወንጌል አማኝ በአቶ ማሬ ዳያ አስተባባሪነት የመጀመሪያዋ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በ1943 ዓ.ም. ተተከለች። ሁለተኛዋ አጥቢያ በሊሞ ቀበሌ በ1944 ዓ.ም. ተተከለች።

በ1945 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ የምሥራቹ ቃል ለአማሮ ሕዝብ ተሰበከ። አቶ ዳይና ከርዲ የተባሉ ሰውና ቤተሰባቸው የመጀመሪያ አማኞች ሆኑ። ከሌሎች ስድስት ሰዎችም ጋር ተጠምቀው የአማሮ

አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን የመጀመሪያ አጥቢያ ተከሉ። የአማሮ እና የቡርጂ ቤተ ክርስቲያናት እስከ 1972 ዓ.ም. ድረስ በአንድ ማሕበር ተጠቃለው ሲሠሩ እንደነበር ይታወቃል።



የይርጋ ጨፌ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች

የጌዴኦ፣ ይርጋጨፌ፣ አማሮ–ቡርጂ ቤተ ክርስቲያናት እጅ ለእጅ በመያያዝ ወንጌልን ለገዛ ወገኖቻቸውና ከክልላቸውም ውጭ በመስበክ ረገድ ዓይነተኛ ምሳሌ ናቸው። በተጠቀሱት አካባቢዎች በ1960ዎቹ መጨረሻ ከ300 ያላነሱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት የነበሩ ሲሆን ኃይላቸውን በጋራ በማስተባበር መንፈሳዊ በረከቶቻቸውን የሚካፈሉበት የኅብረት ጽሕፈት ቤትም በማቋቋም ግንባር ቀደም ናቸው። በዚህ አንጻር በደቡብ ኢትዮጵያ የማይናቅ ማሕበራዊ ኃይል በመሆን በመንግሥት አስተዳደርና በፖለቲካውም ዘርፍ ተደማጭነት አትርፈዋል።



የይርጋ ጨፌ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች

# 17. በመጨረሻ ወደ መጀመሪያው

## 1ኛ. ምዕራብ ኢትዮጵያ

የአቢሲኒያን ፍሮንቲየር ሚሽን መሥራችና በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የኤስ. አይ. ኤም ሚስዮን መልእክተኛ ዶ/ር ቶማስ ላምቤ የከፋ ክፍለ ሐገርን የሚያውቋት በ1912 ዓ.ም. በምዕራብ ሱዳን በኩል በመግባት የሳዮን የሚስዮን ጣቢያ ከከፈቱ በኋላ የወቅቱን አልጋ ወራሽ ለመተዋወቅ ወደ አዲስ አበባ በመጡበት ወቅት መሆኑን ከቅጽ አንድ የታሪክ መጽሐፍ ንባብዎ ያስታውሷል።[1]

ላምቤና ባልደረቦቻቸው የካቲት 28 ቀን 1920 ዓ.ም. አዲስ አበባን ለመልቀቅ ጓዛቸውን ሲጠቀልሉ መድረሻቸው ደቡብ ሳይሆን ምዕራብ ኢትዮጵያ በተለይም ጂማ እና አካባቢው እንደሚሆን ገና ከአሜሪካ ሳይነሱ የቀየሱት እቅድ ነበር። በዶ/ር ላምቤ ጥንቁቅነት የተቀየሰው እቅድ በእግዚአብሔር ልዩ ጥንቃቄና ጣልቃ ገብነት ተቃንቶ ራሳቸውን በደቡብ ኢትዮጵያ ጎዳና ላይ ማግኘታቸው እስከ ዛሬ ድረስ ተወርቶ ያልሰለቸ ተአምር አከል ታሪክ ነው።[2]

ሚስዮናውያኑ በጅማ የስብከተ ወንጌል ሥራ ለመጀመር የቻሉት በሆማቾ ( ሲዳማ ) ሶቶና ( ወላይታ) ላምቡዳ( ሃዲያ) ማረቆ፥ ቡልቂ ( ጎፋ) የሚስዮን ጣቢያዎች ከተከፈቱ በኋላ በመጋቢት ወር 1923 ዓ.ም. ነበር የሚስዮኑ ጣቢያ የተከፈተው ያለብዙ ውጣ ውረድ ከአንድ አርመናዊ ቡና ነጋዴ ጥቂት ቤቶች የተሠሩበትን ሰፊ መሬት በመግዛት ነበር። ከጥቂት ወራትም በኋላ የኤስ. አይ. ኤም ሰባተኛው የሰበካ ጣቢያ በአጋሮ ተከፈተ። የአጋሮን የሰበካ ጣቢያ ለመክፈት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉት ሚ/ር ሮድ የተባሉት የዶ/ር ላምቤ ረዳት እንደሆኑ ታውቋል።[3]

---

1. ወንድዬ ዓሊ፥ 1990 ዓ.ም. ገጽ 80–81
2. ዝኒ ከማሁ ገጽ 85
3. Fargher. 1996 p. 99

በተቀራራቢ ጊዜያት በምዕራብ ኢትዮጵያ በጎማ ወረዳ የወንጌል ሥራ ስርጭት ተጀምሮ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ።[4]

ከፋ የአባጅፋር አገር ጠንካራ የሙስሊሞች መናኸሪያ የመሆኗን ያህል ሚስዮኑ በበኩሉ በቂ ሥነ-ልቦናዊ ዝግጅት ያለማድረጉ ተጨማምሮ እስከ ጣሊያን ወረራ ድረስ የተገኘው ውጤት ተስፋ አስቆራጭ ነበር።[5] ይልቁንም በጅማ ከተማ የተጀመረው የጤና ጥበቃ አገልግሎት ብዙዎቹን ሊስብ በመቻሉና ከተሜውም በአብዛኛው አማርኛ ተናጋሪ ስለነበር በኦሮምኛ ወንጌል መመስከራቸውን በማቆም ሚስዮናውያኑ እንደገና አማርኛ ለማጥናት ተገድደው ነበር። በመጨረሻም የጣሊያን ባለሥልጣኖች በአጋሮ እና በጅማ ያሉት የሰበካ ጣቢያዎች እንዲዘጉ አዘዙ። ህዳር 24 ቀን 1929ዓ.ም. ሚስተር ሻንክና ባለቤታቸው፥ ሚስተር ፒፕግራስ እና ባለቤታቸው፥ ኤርማ ሸንክ፥ ሜሪ ቢም የተባሉት ሚስዮናውያን ወደ አዲስ አበባ ተላኩ። ሥራው ቆመ። በወንጌል አምነው የነበሩት በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችም እድል ፈንታ አልታወቀም።

ወራሪው የጣሊያን ሠራዊት ከኢትዮጵያ ከተባረረ በኋላ እና ሁሉ ነገር የቀድሞ መልኩን እንዲይዝ ጥረት በሚደረግበት አፍላ ወቅት ላይ ኤስ.አይ.ኤም በ1946 ( እ.ኤ.አ) በጅማ፥ በቦንጋ፥ በአጋሮ እንዲሁም አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ በሳጃ ጣቢያዎችን በመክፈት ክሊኒኮችና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በማቋቋም እንቅስቃሴ ጀመረ። ከዚሁ ጎን የወላይታ የከምባታና ሃዲያ ቤተ ክርስቲያናት ባህል ዘለል ወንጌላውያን በመሰማራታቸው በርካታ ሕዝብ የምሥራቹን ቃል ሰማ። በተጠቀሱት በታዎች ላይ በ8 ዓመታት ውስጥ 8 አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ተተከሉ። እነዚህም ናቸው አሁን በምዕራብ ኢትዮጵያ ለሚገኙት 286 ያህል የቃለ ሕይወት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት መነሻ የሆኑት፤ ዝርዝሩን ከሠንጠረዡ ይመልከቱ።

[4]. Ibid P. 137

[5]. Ibid p. 138

የየም አካባቢ ሕዝብ ለወንጌል ያለው ምላሽ ከፍ ያለ ስለነበር ግማሾቹ አጥቢያዎች የተተከሉት በዚያው አካባቢ ነበር። የየም( ሳጃ) ማኅበር የወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበርን ከመሠረቱት ቀዳማይ ማኅበሮች ( አውራጃዎች) መካከል አንዱ ስትሆን በ1949 ዓ.ም. በተደረገው የአንድነቱ ጉባኤ ላይ አቶ ጋሩሙ ገብረወልድ እና አቶ ሐብተማርያም በሚባሉት እንደራሴዎቿ ተወክላ እንደነበር በወቅቱ የተመዘገበው ቃለ ጉባኤ ያረጋግጣል። የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ዋና ጸሐፊ አቶ ተከሉ ወልደ ጊዮርጊስ የዚቹ ማኅበር ፍሬ እንደሆኑ ይታወሳል።

በጅማ ዙሪያ ያሉት አጥቢያዎች ማኅበር በአገር አቀፉ የአንድነት ጉባኤ ላይ መሳተፍ የጀመረው ጥር 30 ቀን 1955 ዓ.ም. አንስቶ ነው። ጅማ ከዚህ ሌላ የምትታወቀው በ1960 ዓ.ም. ሥራ በጀመረው እና ምላተ ጸጋ የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ” በተሰኘው ተቋም ነው።

## የቤተ ክርስቲያናት ዕድገት በምዕራብ ኢትዮጵያ

| ዘመን ከ–እስከ | ጅማ | አጋሮ | ከፋ | የም ሳጃ | ገዋታ | ጋም ቤላ | ሚዛ ን | መቱ | ጥቅም ት እሸት | ድም ር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1940–49 | 2 | 1 | 1 | 4 | – | – | – | – | | 8 |
| 50–49 | 6 | 1 | 1 | 7 | – | – | – | – | | 15 |
| 60–69 | 11 | 5 | 13 | 7 | – | – | – | – | | 36 |
| 70–79 | 5 | 2 | 4 | 2 | 1 | – | – | – | | 14 |
| 80–89 | 38 | 27 | 100 | 19 | 9 | 8 | 22 | 5 | 28 | 266 |
| 1990 | 54 | 27 | 100 | 21 | 11 | 8 | 22 | 5 | 38 | 286 |

## 2ኛ. ሰሜን ኢትዮጵያ

ክርስትና በኢትዮጵያ የተጀመረው የሥነ መለኮት አዋቂው ኦሪጂን እንደሚለው በቅዱስ ማቴዎስ ይሁን፥ ወይንም በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ እንደተመዘገበው በኢትዮጵያዊው ጀንደረባ፥ ወይንም ታሪክ እንደሚያረጋግጠው በፍሬምናጦስና ሲድራኮስ፤— አነሳሱና እና እድገቱ የሰሜን ኢትዮጵያ ክፍል እንደሆነ የተረጋገጠ ነው።

የ1600 ዓመታት የክርስትና ታሪክ ባላት አገር፥ በአርባ ሺህ ያህል የሚቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናትና ደብሮች፥ ገዳሞች ተተክለው የሕዝቡ የዕለት በዕለት የህይወት እሳቤ ማእከል በሆኑበት ምድር፥ ከአንድ መቶ ዓመታት ወዲህ ስለተተከሉ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያናት ለመተረክ ስንተጋ መሠረታችንን እንዳንስት መጠንቀቅ ያሻል።

ክርስትና በኢትዮጵያ የሰሜኑ ክፍል ተማክሎ በኖረበት ዘመን በተለይም ከ300–700 ዓ.ም. ታላቅ ውስጣዊ እንቅስቃሴ ያደረገበት ዘመን ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ከግሪክና ከአረማይክ ቋንቋዎች ወደ ግዕዝ የተተረጎሙበት፥ አዲሱ ሃይማኖት ለአዲስ ቋንቋና ባህል መንቃት መነሻ የሆነበት፥ ቤተ ክርስቲያኒቱም በጊዜው የዓለም ክርስትና ማእከሎች ቁስጥንጥኒያ፥ አንጾኪያ እና እስክንድሪያ እውቅናን የተጎናጸፈችበት ዘመን ነው።

ተከታታዩን 400 ዓመታት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አዋቂዎች "የዝምታ ዓመታት" ይሏቸዋል። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከውጭው ዓለም ተለይታ የኖረችበት ነገር ግን ቅሬታዋ ጭራሽ ያልጠፉበት እንዲያውም በጣም "አገረ ሰባዊ"የ ሆነችበት ዘመናት ናቸው።[1]

---

[1] . Fargher. 1996 p. 6

ከ1220–1500 ያሉት ዓመታት ደግሞ የመነቃቃትና የመስፋፋት ዓመታት ናቸው። የክርስትና ድንበርም ከሰሜንና ከማእከላዊው ግዛቶች ወደ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ ግዛቶች የተስፋፋበት እንዲሁም አዎንታዊ አሻራውን ጥሎ ያለፈበት ዘመን ነው። በዚህ ረገድ ከቤተ ክኅነት የአቡነ ተክለሃይማኖት መንፈሳዊ ተጋድሎ በአገር ውስጥም በውጭም በርካታ አድናቂዎች እንዳሉት ማስታወሱ ተገቢ ነው። ከነገሥታቱም አፄ ይኩኖ አምላክ፥ አፄ አምደ ፅዮን፥ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ኹነኛዎቹ ተጠቃሾች ናቸው።

ጥንታዊቷ ቤተ ክርስቲያን በአገር ውስጥ ከአደረገችው ጥረት የበለጠ አገሪቱን ለስልታዊ ጥቅሞቻቸው ሲሉ ለመቆጣጠር ወይም ለማፈራረስ ሃይማኖትን ተገን አድርገው ከሚመጡት ኃይሎች ጋር ለዘመናት ያላቋረጠ መከላከል ስታደርግ መቆየቷ በታሪክ ፊት የማይደበዝዝ ሞገስ ሆኖላታል። በቱርኮች አነሳሽነት ከምሥራቅ ኢትዮጵያ ተነስቶ ከ1528–1540 ድረስ አገሪቱን ያመሰው እና መተኪያ የማይገኝላቸው የአገሪቱን ቅርሶች ያወደመው ግራኝ መሃመድ አንዱ ተጠቃሽ ነው።

ይህች ቤተ ክርስቲያን እኒህን ሁሉ ፈተናዎች ተቋቁማ በሰሜን አፍሪቃ ተነሥተው እንደ ከሰሙት የሐዋርያት ዘመን ቤተ ክርስቲያናት ሳትከስም እና የክርስትና ታሪክ በኢትዮጵያ እንዳይቋረጥ ያደረገችው አስተዋጽኦ በራሱ በበጎ ሊታይ ይገባዋል።

> *ከውጭው ዓለም የወንጌል አገልጋዮች በአረማውያንና በሌሎች ሃይማኖት ተከባ በመኖሯ ልዩ የሆኑ የራሷን ልምምዶችና ባህሎች ያዳበረችውን ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆኑ እንደምታዎች በመድረስና ተሐድሶን ፈጥሮ በእርሷም በኩል ሕዝቡን ለማግኘት ለ400 ዓመታት ያህል ሙከራ ማድረጋቸው ሌላው ተግዳሮት ነበር።*[2]

---

[2] . ወንድዬ ዓሊ 1990 ገጽ 39–50

ከብዙ አድካሚ ሙከራዎች በኋላ የኤስ.አይ.ኤም. ሚስዮን በሰሜን ኢትዮጵያ የስብከተ ወንጌልና የማሕበራዊ ግልጋሎት መስጫ ጣቢያዎችን ከፍቶ ሁለንተናዊ አገልግሎት ለመስጠት ተግባራዊ እርምጃ የወሰደው በቅድመ ጣሊያን ወረራ በ1926 ዓ.ም. ነበር። አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ በ1927 ዓ.ም. በላስታ ሚስዮናውያንን ለማስፈር ተቻለ። የሚያበረታታ የመሠረተ ትምህርት ጀምረው ለጥቂት ሰዎችም ወንጌልን እንደሰበኩ በጣሊያን ወረራ ምክንያት ተጨናገፈ። ከላስታ ሌላ በቅድመ ጣሊያን ወረራ በባህር ዳርና በጎንደር ጣቢያዎችን ለመክፈት ዶ/ር ላምቤ ሰፋ ያለ አሰሳዊ ጉዞ እንዳከናወኑ ታውቋል።

የጣሊያን ወረራ ከአከተመ በኋላ ኤስ.አይ.ኤም. እንደገና ወደ አገር ውስጥ ከገባበት ማግሥት አንስቶ በሰሜን ኢትዮጵያ ለመሥራት ጠንካራ ፍላጎት አሳይቷል። ስብከተ ወንጌልን ከማሕበራዊ አገልግሎት በማጣመር ጣቢያ የመሠረተባቸው አካባቢዎች ቀጥሎ ተዘርዝረዋል።

ኤስ. አይ. ኤም. በሰሜን ኢትዮጵያ

| ሥፍራው | የተከፈተበት ዘመን(እ. ኤ. አ) | እንቅስቃሴ |
|---|---|---|
| አላማጣ | 1954 | ክሊኒክ፥አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፥ስብከተ ወንጌል |
| አሥመራ | 1952 | ክሊኒክ፥አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፥ ስብከተ ወንጌል |
| አሰብ | 1952 | ስብከተ ወንጌል፥ከ2 ዓመት በኋላም ተዘጋ |
| ባህር ዳር | 1965 | እጓለማውታን፥ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት |
| | | የአማርኛ ት/ቤት ለሚስዮናውያን |
| ደብረ ብርሃን | 1953 | የሥጋ ደዌ ሕክምና፥ ጠቅላላ ሆስፒታል |
| ደሴ–በሩሜዳ | 1954 | አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፥ ስብከተ ወንጌል |
| ማይጨው | 1947 | ክሊኒክ፥ አንደኛ ድረጃ ት/ቤት ስብከተ ወንጌል |
| ናቅፋ | 1955 | ክሊኒክ፥ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፥ ስብከተ ወንጌል |

በአጠቃላይ የፕሮቴስታንት ተቋሞች በተለይም የኤስ. አይ. ኤም. ሚስዮን በሰሜን ኢትዮጵያ ያደረገው ስብከተ ወንጌል እንደ ደቡቡ እና የምዕራብ ኢትዮጵያ ክፍል ለምን ውጤት እንደላሳየ ለመረዳት ጠበቅ ያለ ጥናት ይጠይቃል። በ1986 ዓ.ም. የተደረገውን የሕዝብና ቤት ቆጠራ ውጤት መነሻ በማድረግ የተዘጋጀ አንድ መረጃ እንደሚጠቁመው በይህ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ክፍል የሚገኙት የወንጌላዊት እምነት ተከታዮች ብዛት ከ0.1% በታች ነው። ከደቡብ 34.9%ሲወዳደር በጣም ጥቂት መሆኑን እንገነዘባለን።

ሕዝቡ ለወንጌል ቃል ምላሽ ያለመስጠቱ ምክንያቶች በርካታ የመሆናቸውን ያህል ከባህላዊ፥ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ በተለይም ከመሬት ስሬት አንጻር የሚተነተኑ ናቸው። ጥቂቶቹን ለመጥቀስ ያህል እነሆ፡–

በመጀመሪያ ደረጃ ነባሩ ሃይማኖት የሕዝቡ ማንነት መገለጫ የታሪኩ እና የቅርሱ ቤተመዛግብት በመሆኑ ሃይማኖቱን ከቶም ለጥያቄ የማቅረብ ልማድ አልነበረውም። በሁለተኛ ደረጃም ላለፉት ብዙ መቶ ዓመታት በአገሪቱ ላይ የተቃጡት የውጭ ወረራዎች በሰሜን የአገሪቱ ክፍል በኩል የተከሰቱ ከመሆናቸውም በላይ የአንዳንዶቹ ጦርነቶችም መንስኤ ከሃይማኖት ቅንዓት ጋር የተገናኘ መሆኑ እርግጥ ነው። ይህም ሕዝቡ አገሩንና ሃይማኖቱን ሲከላከል እንጂ በአገሩና በሃይማኖቱ ያለመደራደርን በሌላ በኩልም የተከላካይነትን ባህል እንዲያዳብር አድርጎታል።

ከዚህ አንጻር የጦርነቱ ሰለባ የድሉም ተካፋይ ሆኖ የኖረው ሕዝብ ለውጭ አገር ሰዎች ( ለፈረንጆች ) እና ከእነርሱ ጋር ተያይዞ ለመጣው አስተሳሰብና አስተዋፅኦ ሁሉ ደመ ነፍሳዊ ጥርጣሬ ንቀትና ጥላቻ ቢያሳይ እንደ እንግዳ ነገር ሊቆጠር አይገባም። እባብ የነደፈው በልጥ ይበረግጋል እንዲሉ። ከላይ ከተጠቀሰው ነጥብ አኳያ የወንጌል አገልጋዮች በበጎ ምግባር የታገዘ ምሳሌነት ያለው የተጠና እርምጃን በመራመድ ጥርጣሬው የሚለዝብበትን መንገድ ማቅናት ይጠበቅባቸዋል።

በሦስተኛ ደረጃ ከጣሊያን መባረር በኋላ በተለይም ከምእተ ዓመቱ አጋማሽ በኋላ በአገሪቱ ውስጥ የተሰማሩት ወንጌላዊት ቤተ እምነቶች ባህልንና ልማድን ከአስተምህሮአቸው እምነት ጋር ለማቻቻል በቂ ጥናትና ዝግጅት ያለማድረጋቸው እና ከአማኒያኑ ፍጹም መለየትን ስለሚጠብቁ የአማኒያኑን ቀንበር እንዳከበደው ሁሉ ወንጌላዊ ያልሆነውን ሕብረተሰብ ለመሳብ እንዳልቻሉም እሙን ነው።



ባለፉት መቶ ዓመታት የወንጌል እንቅስቃሴ ታሪክ ይህንን የባህል አጥር ጥሰው፥ የተጫኑባቸውን መከራ ታግሰው፥ በገዛ አገራቸው በባይተዋርነት ያለፉትን እነ አለቃ ዘነብ፥ እነ አለቃ ታዬ ገብረማሪያም፥ እነ ተሰማ ኃይሉ እነ አናሲሞስ ነሲብ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን የወንጌል አማኞች ታሪክ ለመተረክ ጊዜና ልዩ መሰጠት የሚጠይቅ ስለሆነ ፅናት የሆናቸውን አምላክ እየባረክን እንዲሁ እንዘክራቸዋለን።

*አቶ ሺፈራው አየለ*

በዚሁ አንጻር እጅግ ከባድ የሆነውን የባህል ቀንበር በፅናት ተሸከመው እለታዊ የኑሮ እርምጃቸውን አሸማቀው ከከፍለ ዘመኑ አጋማሽ ወዲህ የሰሙትን የምሥራች ቃል ጌዜው በደረሰ ጊዜ በሙላት እንዲሰበክ፥አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትም እንዲተከሉ ምክንያት የሆኑትን ቅሬታዎቹን እናስባለን። በጎጃም ( ዳንግላ) እነ አቶ ሺፈራው አየለ፥ በትግራይ (በማይጨው )እነ አቶ አድነው ወልደ ገብርኤል፥ በወሎ (ቦሩ



ዋልን።    አቶ ሽፈራው አየለ

ሜዳ) እነ አቶ አህመድ፥ አቶ ብርሃኑ እና አቶ አምደየሱስ የመሳሰሉትን ስናስታውስ «ትዕግሥትና ፅናት» ሥጋ ለብሰው የተከሰቱልን ያህል እንደነቃለን። በምድሪቱ ላይ የተዘራው የማይጠፋው ዘር አንድ ቀን በሙላት በቅሎ፥ በመልካም የወንጌል ገበሬዎች እጅ ታርሞ ለደቡብ ሕዝብ እንደሆነለት በረከት ለሰሜኑም እንደሚደርስ የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እምነት ነው።

*የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት አኃዛዊ እድገትና ስርጭት የሚያሳይ ሠንጠረዥ*

| ዘመን (እ.ኤ.አ) | 1942 | 1945 | 1950 | 1960 | 1965 | 1970 | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወላይታ | 80 | 150 | 200 | 250 | 334 | 340 | 493 |
| ከምባታና ሃዲያ | 70 | 100 | 145 | 170 | 216 | 312 | 330 |
| ሲዳማ | 0 | 0 | 3 | 26 | 56 | 139 | 191 |
| ጌዴኦ/ዲላ | 0 | 0 | 1 | 18 | 36 | 94 | 158 |
| ቡርጂ | 0 | 0 | 0 | 1 | 40 | 81 | 85 |
| ጋሞ | 0 | 0 | 5 | 30 | 42 | 75 | 100 |
| ጎፋ–ቡልቂ | 0 | 0 | 2 | 20 | 40 | 67 | 123 |
| ሐመር ባኮ | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 24 | 44 |
| ኩሎ/ዳውሮ | 0 | 0 | 8 | 10 | 12 | 20 | 28 |
| የም | 0 | 0 | 0 | 0 | 4 | 7 | 9 |
| አርሲ ሻሸመኔ | 0 | 0 | 2 | 8 | 10 | 12 | 25 |
| ጫቦ | 0 | 0 | 0 | 0 | 1 | 3 | 5 |
| ሌሎች | 0 | 0 | 3 | 5 | 8 | 10 | 12 |
| ድምር | 150 | 250 | 369 | 538 | 800 | 1184 | 1603 |

## የምእመናን ቁጥር በወላይታ ቤተ ክርስቲያን

| ዘመን(እ.ኤ.አ) | የአጥቢያቤተክርቲያናት ብዛት | የተጠመቁ ምእመናን | አማካይ ብዛት ለአንድ አጥቢያ |
|---|---|---|---|
| 1945 | 150 | 15,000 | 100 |
| 1950 | 200 | 25,000 | 105 |
| 1955 | 250 | 32,000 | 132 |
| 1960 | 334 | 52,000 | 156 |
| 1965 | 340 | 66,000 | 194 |
| 1970 | 493 | 81,000 | 164 |

## የሲዳሞ ክፍለ ሐገር ቤተ ክርስቲያናት ገጽታ

| ዘመን (እ.ኤ.አ) | 1950 | 1955 | 1960 | 1965 | 1970 |
|---|---|---|---|---|---|
| ሲዳማ– ወንዶ | 3 | 26 | 56 | 139 | 191 |
| ጌዴኦ –ዲላ | 1 | 17 | 28 | 74 | 89 |
| ጌዴኦ–ይርጋጨፌ | 0 | 1 | 8 | 20 | 69 |
| ቡርጂ | 0 | 1 | 40 | 81 | 85 |
| ድምር | 4 | 45 | 132 | 314 | 434 |

## የጋሞ ጎፋ ክፍለ ሐገር ቤተ ክርስቲያናት ገጽታ

| ዘመን (እ.ኤ.አ) | 1950 | 1955 | 1960 | 1965 | 1970 |
|---|---|---|---|---|---|
| ጋሞ | 5 | 30 | 42 | 75 | 100 |
| ጎፋ | 2 | 20 | 40 | 67 | 123 |
| ሐመርባኮ | – | 0 | 1 | 24 | 44 |
| ድምር | 7 | 50 | 83 | 166 | 267 |

ምንጭ፡– Cotterll, 1973 p 174

## የቤተ ክርስቲያን እድገት በለውጡ ዋዜማ እና መባቻ

| ዘመን (እ.ኤ.አ) | የቤተ ክርስቲያናት ብዛት | የዕድገት ዘመን | ዓመታዊ የዕድገት መጠን |
|---|---|---|---|
| 1965 | 1184 | 1966–1970 | 7.08% |
| 1970 | 1603 | 1971–1974 | 6.66% |
| 1974 | 2030 | 1975 | 13.30% |
| 1975 | 2300 | 1976 | 8.69% |
| 1976 | 2500 | 1977 | 8.00% |
| 1977 | 2700 | | |

ምንጭ፡- Brant Haward. Church and Mission under fire in Ethiopia. 1974-197
unpublished.